Ontario

የጤና ሚኒስቴር

# ከኮቪድ-19 ክትባትዎ በኋላ

ስሪት 2.0 ማርች 29፥ 2021 ዓ.ም.

**በሚቀጥሉት ቀናት ውስጥ ምን ልጠብቅ ይገባል?**

- የተለመዱ ጎጂ ጎኖች መርፌ የተወጋው ቦታ ላይ ሕመም፥ መቅላት፥ እብጠት፥ ድካም፥ ራስ ምታት፥ የጡንቻ ሕመም፥ ብርድ ብርድ ማለት፥ የመገጣጠሚያ ሕመምና መለስተኛ ትኩሳት።
- ከባድ ጎጂ ጎኖች ያልተለመዱ ናቸው። ክትባቱን በወሰዱ በሶስት ቀን ውስጥ ከሚከተሉት አሉታዊ ምላሾች ውስጥ ማናቸውም ቢያጋጥሙዎት፥ ዶክተርዎ ጋር ወይም ነርስ ፕራክቲሽነር ጋር ይደውሉ ወይም በቅርብ ወደሚገኘው ድንገተኛ ሕክምና ክፍል ይሂዱ፡- ሽፍታ፥ የፊትዎ ወይም የአፍዎ እብጠት፥ የመተንፈስ ችግር፥ ፈዛዛ ቀለምና ከባድ ራስ ማዞር፥ ከፍተኛ ትኩሳት (ከ40˚C በላይ)፥ መንቀጥቀጥና አዙሪት ወይም ሌላ ከባድ ምልክቶች (ለምሳሌ "በመርፌ እንደመጠቅጠቅ" ዓይነት ስሜት ወይም መደንዘዝ)።
- የAstraZeneca/COVISHIELD (አስትራዜኔካ/ኮቪሺልድ) ክትባት በጣም ያልተለመደ ከሆነ Vaccine-Induced Prothrombotic Immune Thrombocytopenia (VIPIT) (በክትባት የሚመጣ የደም መርጋት የሚያመጣ ኢምዩን ትሮምቦሲቶፔኒያ) የሚባል ጎጂ ጎን ጋር ተያይዟል። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ከሚከተሉት ውስጥ ማናቸውንም ምልክቶች ካሳዩ ወዲያውኑ ወደ ሐኪም ይሂዱ፡- የትንፋሽ እጥረት፥ የደረት ሕመም፥ ክንድ ወይም እግር ላይ እብጠት ወይም የቅዝቃዜ ስሜት፥ የማያቋርጥ ሆድ ሕመም፥ ከባድ ወይም እየባሰ የሚሄድ ራስ ምታት ወይም ብዥ ያለ እይታ ወይም በርካታ ትናንሽ ቁስሎች፥ ከቆዳ ሥር ቀይ ወይም ሐምራዊ የደም ቋጠሮዎች።

**አሁንም የጤና ጥበቃ የኮቪድ-19 እርምጃዎችን መከተል አለብኝ ወይ?**

- ክትባቱ እራስዎን ከኮቪድ-19 መከላከያ ተጨማሪ መንገድ ነው። ማንኛውንም የኮቪድ-19 ክትባት ዙር ከወሰዱ በኋላ የኮቪድ-19 እርምጃዎችን መከተል መቀጠል አለብዎት፥ ለምሳሌ ማስክ ማድረግ፥ አካላዊ ርቀት መጠበቅና እጆችን መታጠብ።
- የኮቪድ-19 ምልክቶች መኖራቸውን ይከታተሉና ምልክት ከታየ ምርመራ ያድርጉ።

**ለሁለተኛው ዙር ክትባት መቼ ነው መመለስ ያለብኝ?**

- ሙሉ በሙሉ የመቋቋም ዓቅም ለማግኘት ሁለት የክትባት ዙሮች ያስፈልግዎታል። ይህ የመጀመሪያዎ የኮቪድ-19 ክትባትዎ ከሆነ፥ በክሊኒኩ ደንብ ወይም በቀጠሮ መያዣው ሥርዓት መሠረት ሁለተኛ ዙር መውሰድዎን ያረጋግጡ። ወደ ሁለተኛ ቀጠሮዎ ሲሄዱ ዛሬ የተሰጥዎትን የክትባት ደረሰኝ በወረቀት ይዘው ይሂዱ።